TIENS 天狮

CROWD 1

FIAS

etcare

# ፒራሚዳዊ ስልት ባላቸው ንግዶች/ቢዝነሶች ላይ መሳተፍ በሸሪዓ እይታ እንዴት ይታያል?

### ፓምፕሌት ቁጥር 2

ኢቲኬርን የመሰሉ የሰንሰለት የግብይት ስርዓቶች ክልክል መሆናቸው ፓመፕሌት ቁጥር 1 ላይ ቁርዓን እና ሃዲስን መሰረት በማድረግ ቢገለፅም ይህን ቢዝነስ ሃላል እንዲሆንላቸው የሚፈልጉ ወንድም እና እህቶች ቢዝነሱን ሃላል ለማድረግ ይህ ግብይት ልክ እንደ ድለላ ስራ ወይም እንደ ስጦታ መታየት ይችላል በማለት መከራከሪያ ያቀርባሉ፡፡ የፈትዋ ምክር ቤቱ ለዚህም የሚከተለውን ምላሽ ሰጥቶበታል

**<u>እውን የኔትዎከር ማርኬቲንግ የድለላ ስራ ነውን??</u>**

ይህን ግብይት ልክ እንደ ድለላ ስራ አይነት እንደሆነ መመልከቱ ትክክል አይደለም፡፡ ኔት ወርክ ማርኬቲንግ ከድለላ ወይም ከኮሚሽን ስራ በሚከተሉት ነጥቦች ይለያያሉ፡-

- ድለላ ማለት ደላላው ምርቱን በመሸጡ ገንዘብ የሚቀበልበት ስራ ሲሆን የኔትዎርክ ግብይት ግን ተሳታፊው ምርቱን ለመሸጥ ለሻጩ ድርጅት የገንዘብ ክፍያ የሚከፍልበት አሰራር ነው፡፡
- የድለላ ስራ በትክክልም በቀጥታ አላማው ምርቱን መሸጥ ሲሆን የኔትዎርክ ማርኬቲንግ ግን ዋና አላማው የግብይቱን አባልነት መሸጥ እንጂ ምርቱን መሸጥ አይደለም፡፡
- በኔትዎረክ ማርከቲንግ ላይ አንዱ አባል ለአንዱ ይሸጥለታል፣ሌላው ደግሞ ለሌላው ሰው ይሸጥለታል፡፡ ይህ ሰው ደግሞ ለሌላ ተሳታፊ ይሸጥለታል፡፡ እንዲህ እያለ የሚቀጥል አሰራር ሲሆን ድለላ ግን በቀጥታ ምርቱን ለፈላጊው እና ለተጠቃሚው የሚሸጥበት አሰራር ነው፡፡
- በኔትወርክ ማርኬቲንግ ላይ ከላይ ያለው አባል ከስሩ ላሉት አባላቶች ከሸጠላቸው ቡሃላ ከስር ያሉት አባላቶች በተራቸው ለሌሎች በሸጡ ቁጥር ከላይ ያለው አባል ምንም ሳይለፋ ከፍተኛ የሆነ ኮሚሽን ሌሎች በሱ ስር ያሉት በሸጡ ቁጥር ያገኛል፡፡ በድለላ ስራ ላይ ግን አንድ ጊዜ ለተጠቃሚው ከሸጠ ቡሃላ ለሌሎች ቢሸጥ ደላላው የሚያገኘው ገንዘብ አይኖርም፡፡ በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት በጣም ግልፅ እና ሰፊ ነው፡፡

**<u>እውን የኔትዎከር ማርኬቲንግ የድለላ ስራ ነውን??</u>**

ይህን ግብይት ልክ እንደ ድለላ ስራ አይነት እንደሆነ መመልከቱ ትክክል አይደለም፡፡ ኔት ወርክ ማርኬቲንግ ከድለላ ወይም ከኮሚሽን ስራ በሚከተሉት ነጥቦች ይለያያሉ፡-

- ድለላ ማለት ደላላው ምርቱን በመሸጡ ገንዘብ የሚቀበልበት ስራ ሲሆን የኔትዎርክ ግብይት ግን ተሳታፊው ምርቱን ለመሸጥ ለሻጩ ድርጅት የገንዘብ ክፍያ የሚከፍልበት አሰራር ነው፡፡



- የድለላ ስራ በትክክልም በቀጥታ አላማው ምርቱን መሸጥ ሲሆን የኔትዎርክ ማርኬቲንግ ግን ዋና አላማው የግብይቱን አባልነት መሸጥ እንጂ ምርቱን መሸጥ አይደለም፡፡
- በኔትዎረክ ማርከቲንግ ላይ አንዱ አባል ለአንዱ ይሸጥለታል፣ሌላው ደግሞ ለሌላው ሰው ይሸጥለታል፡፡ ይህ ሰው ደግሞ ለሌላ ተሳታፊ ይሸጥለታል፡፡ እንዲህ እያለ የሚቀጥል አሰራር ሲሆን ድለላ ግን በቀጥታ ምርቱን ለፈላጊው እና ለተጠቃሚው የሚሸጥበት አሰራር ነው
- በኔትወርክ ማርኬቲንግ ላይ ከላይ ያለው አባል ከስሩ ላሉት አባላቶች ከሸጠላቸው ቡሃላ ከስር ያሉት አባላቶች በተራቸው ለሌሎች በሸጡ ቁጥር ከላይ ያለው አባል ምንም ሳይለፋ ከፍተኛ የሆነ ኮሚሽን ሌሎች በሱ ስር ያሉት በሸጡ ቁጥር ያገኛል፡፡ በድለላ ስራ ላይ ግን አንድ ጊዜ ለተጠቃሚው ከሸጠ ቡሃላ ለሌሎች ቢሸጥ ደላላው የሚያገኘው ገንዘብ አይኖርም፡፡ በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት በጣም ግልፅ እና ሰፊ ነው፡፡

**<u>የኔትወረክ ማርኬቲንግ ከስጦታ ወይም ከጉርሻ(Bonus) ጋር ተመሳሳይ ነውን??</u>**

ይህ አሰራር ከስጦታ እና ከጉርሻ ጋር ማመሳሰሉ ትክክል አይደለም፡፡ ይህ አሰራር ከስጦታ ጋር ተመሳሳይ ነው ብለን ብንቀበለው እንኳ ሁሉም ስጦታዎች በሸሪዓው የተፈቀዱ አይደሉም፡፡ ለምሳሌ ተበዳሪ ለአበዳሪው የሚሰጠው ስጦታ እንደወለድ ነው የሚቆጠረው፡፡

አብደላህ ኢብን ሰላም ለ አቡ ቡረዳህ(አላህ መልካም ስራቸውን ለሁለቱም ይውደድላቸው) እንዲህ ብሎታል፡-"ወለድ በሰዎች ዘንድ የተስፋፋበት ምድር ላይ ነው ያለኸው፡፡ በአንድ ሰው ላይ ብድር ካለህ ወይም መብት ካለህ ያ ሰው ላንተ የስንዴ ክምር ወይም ክምር ቀለብ ወይም ሌላ ነገር ከሰጠህ ሪባ ወይንም ወልድ ነው "፡፡ (ቡኻሪ በሷሂህ ሃዲሳቸው ዘግበውታል)

የስጦታዎች መፈቀድ መሰረት ያደረገው ስጦታው በሚሰጥበት ምክንያት ወይም አላማ ላይ ነው፡፡ በአንድ ወቅት ነብዩ ሰለላሁ አለይሂ ወሰላም ዘንድ የዘካ ሰብሳቢው ወደሳቸው በመምጣት "ይህ ላንተ ነው ይህ ደግሞ ለኔ ስጦታ የተሰጠኝ ነው" አላቸው፡፡

ነብዩም ሲመልሱ "ለምን እናት እና አባትህ ቤት ተቀምጠህ ስጦታ እንደሚሰጥህ እና እንደማይሰጥህ አታይም ነበር" በማለት ተናግረውታል፡፡ (ቡኻሪ እና ሙስሊም ዘግበውታል)

በዚህ ግብይት የሚሰጠው ኮሚሽን ምንም አይነት ስያሜ ይሰጠው፣ ስጦታም ይባል ሌላ ነገር የኮሚሽን ክፍያው የሚሰጠው ወደ ሰንሰለት(ኔትዎርክ) ግብይቱ በመቀላቀላቸው ብቻ ነው፡ ይህ የግብይቱን ተፈጥሯዊ ሁኔታም ሸሪዓዊ እይታውን አይቀይረውም፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት ድርጅቶች ጋር የተለያዩ ምርቶችን በመሸጥ ይለያዩ እንጂ የኔትዎርክ ማርኬቲንግ የሚከተሉ ሌሎች ድርጅቶችም አሉ፡ ለምሳሌ አጭበርብረው ካለፉት ውስጥ ቲያንስ:ፊያንስ ስማርተስ ዌይ፣ ጎልድኬስት፣ ሰባት ኮከብ እና ወዘ.. የነዚህ ድርጅቶች የሚሸጡት ምርት ቢለያይም አሰራራቸው ተመሳሳይ በመሆኑ በሸሪአው መነፅር በተመሳሳይ መልኩ የሚታይ ነው የሚሆነው፡፡

ከላይ በማብራሪያው ላይ እንደተቀመጠው በኢቲኬር ድረጅት ውስጥ መስራት ሃራም መሆኑን ተመልክተናል፡፡ በሃራም የሚገኝ ገንዘብ መብላት ምን ያህል የከፋ አደጋ በዱኒያም በአሄራም እንደሚያመጣ የሚታወቅ ነው፡፡

ከላይ በተዘረዘረው መልኩ በኢቲኬር ውስጥ መስራት

*1.የወለድ ገንዘብ በመሆኑ ሃጢያቱ ከባድ ነው፡፡*

ወለድ የሚበሉ ሰዎች የቂያማ ጊዜ ሲነሳ ሸይጣን እንደለከፈው ወይም አውድቅ እንዳለበት ሰው ሆኖ ነው፡፡ በሃላል ንግድ መነገድን አላህ ፈቅዶልናል፡፡ በኢቲኬር መሰሉን የወለድ ስራ ግን ከልክሎናል፡፡ወለድ የሚበላም ሰው መኖሪያው ጀሃነም መሆኑን አላህ ሱብሃነ ወተዓላ እንደሚከተለው ገልፆንልናል፡-

الَّذِينَ يَأْكُلُونَ الرِّبَا لَا يَقُومُونَ إِلَّا كَمَا يَقُومُ الَّذِي يَتَخَبَّطُهُ الشَّيْطَانُ مِنَ الْمَسِّ ۚ ذَٰلِكَ بِأَنَّهُمْ قَالُوا إِنَّمَا الْبَيْعُ مِثْلُ الرِّبَا ۗ وَأَحَلَّ اللَّـهُ الْبَيْعَ وَحَرَّمَ الرِّبَا ۚ فَمَن جَاءَهُ مَوْعِظَةٌ مِّن رَّبِّهِ فَانتَهَىٰ فَلَهُ مَا سَلَفَ وَأَمْرُهُ إِلَى اللَّـهِ ۖ وَمَنْ عَادَ فَأُولَـٰئِكَ أَصْحَابُ النَّارِ ۖ هُمْ فِيهَا خَالِدُونَ ﴿٢٧٥﴾ يَمْحَقُ اللَّـهُ الرِّبَا وَيُرْبِي الصَّدَقَاتِ ۗ وَاللَّـهُ لَا يُحِبُّ كُلَّ كَفَّارٍ أَثِيمٍ

እነዚያ አራጣን የሚበሉ ያ ሰይጣን ከመንካቱ የተነሳ የሚጥለው ሰው (ከአውድቁ) እንደሚነሳ ቢጤ እንጅ (ከመቃብራቸው) አይነሱም፡፡ ይህ እነርሱ መሸጥ የአራጣ ቢጤ ብቻ ነው በማለታቸው ነው፡፡ ግን መሸጥን አላህ ፈቅዷል፡፡ አራጣንም እርም አድርጓል፡፡ ከጌታውም ግሳጼ የመጣለትና የተከለከለ ሰው ለርሱ (ከመከልከሉ በፊት) ያለፈው አለው፡፡ ነገሩም ወደ አላህ ነው፤ (አራጣን ወደ መብላት) የተመለሰም ሰው እነዚያ የእሳት ጓዶች ናቸው፡፡እነርሱ በውስጧ ዘውታሪዎች ናቸው፡ ፡አላህ አራጣን (በረከቱን) ያጠፋል፡፡ ምጽዋቶችንም ያፋፋል፡፡ አላህም ኃጠኢተኛ ከሓዲን ሁሉ አይወድም፡፡ (ሱረቱል በቀራ፡275-276)



የወለድ ገንዘብን የሚበሉትን በቁርአን ላይ አላህን እና መልዕክተኛውን ከመውጋት ጋር አነፃፅሮ ነው አላህ ያስቀመጠው፡፡ ስለዚህ ገንዘቡ አጓጉቶን በኢቲኬር መሰሉ ስራ ላይ የተሰማራን እህቶች ወንድሞች አላህን ፈርተን ከእንደዚህ አይነቱ ቢዝነስ ልንወጣ ይገባናል፡፡

فَإِن لَّمْ تَفْعَلُوا فَأْذَنُوا بِحَرْبٍ مِّنَ اللَّـهِ وَرَسُولِهِ ۖ وَإِن تُبْتُمْ فَلَكُمْ رُءُوسُ أَمْوَالِكُمْ لَا تَظْلِمُونَ وَلَا تُظْلَمُونَ

(የታዘዛችሁትን) ባትሠሩም ከአላህና ከመልክተኛው በኾነች ጦር (መወጋታችሁን) ዕወቁ፡፡ ብትጸጸቱም ለእናንተ የገንዘቦቻችሁ ዋናዎች አሏችሁ፡፡ አትበድሉም አትበደሉምም፡፡(ሱረቱል በቀራ፡279)

2. በሃራም ገንዘብ የሚሰብስብ ሰው የገንዘቡ በረካም ይነሳል፡፡ መልካም ስራ ቢሰራበትም ተቀባይነት አያገኝም፡፡

ኢብኑ መስዑድ ባወሩት ሃዲስ ላይ መልዕክተኛው ሰለላሁ አለይሂ ወሰላም "የአላህ ባሪያ በሃራም ገንዘብን የሚሰበስብ፣ከሱም ላይ ሰደቃ ቢያወጣበት ተቀባይነት አያገኝም፡፡ ወጪ ቢያደርገውም በገንዘቡ ላይ በረካ አይኖርለትም፡፡ ገንዘቡን ትቶ ቢሞትም ወደ ጀሃነም መግቢያ ሰበብ ይሆንበታል፡፡ ንቁ አላህ መጥፎ ስራን በመጥፎ አያብስም፡፡ ነገር ግን መጥፎ ስራን በመልካም ስራ ያብሳል" ብለዋል፡፡(ኢማሙ አህመድ ዘግበውታል)

3.በሃራም ገንዘብ የሚሰበስብ ሰው ዱዓ ቢያደርግም ተቀባይነት አይኖረውም

አቡ ሁረይራ ባወሩት ሃዲስ መልዕክተኛው አንድን ሰው አወሱልን አሉ፡፡" እጁን ወደ ላይ አድርጎ ያ ረብ ያረብ ይላል፡፡ ነገር ግን ምግቡ በሃራም የተገኘ ነው፣የሚጠጣው በሃራም ነው፣ የሚለብሰው በሃራም ነው፣ሰውነቱ ሁሉ የተገነባው በሃራም ሆኖ ሳለ አላህ ዱዓውን እንዴት ይቀበለዋል?" ብለዋል( ኢማሙ ሙስሊም ዘግበውታል)

በኢቲኬር እና መሠል የእሱን አምሳያ ድርጅቶች ብዙ ገንዘብ ይገኛል በሚል ወይም በስራው ላይ ብዙ ሰአት ሰጥታችሁ እየሰራቹህ በብዙ ማባበል እና ማታለል ኮሚሽን ማግኘት የጀመራችሁ ወንድም እና እህቶች ይህን በሸሪዓው የተወገዘ የሃራም ስራ በመሆኑ ይህን ሃራም በመተው ወደ አላህ በመመለስ መልካም የሆነችን ሲሳይ እንዲለግሳችሁ ትማጸኑት ዘንድ አደራ እላለው፡፡

በዚህ ስራ የተሸወዳችሁ እህት እና ወንድሞችም በስራውም ከስራችሁ በአላህ ዘንድም ልትከስሩ አይገባም እና ከዚህ አሳሳች ቢዝነስ እራሳችሁን በማራቅ ወደ አላህ እንድትመለሱ እመክራለሁ፡፡

አላህ ሆይ ከሃራም ሲሳይ ሁሉ ርቀን በሃላሉ የምንብቃቃ አድርገን!!

***በኢቲኬር እና መሰል ድርጅቶች ሀራም ስለመሆናቸው የተናገሩ የፈተዋ ድርጅቶችና ሙፍቲዎች***

ማንኛውም የእስልምና ተከታይ (ዐዋም) ፈትዋ የመሰጠት አቅምም፣ ፍቃድም የለውም፡፡ ፈትዋ ለመስጠት ብዙ መስፈርቶች አሉት፣ ለዚህም ነው የፈተዋ ሰዎች የተለዩ (መተኸሲስ) የሆኑት፡፡

በዚህ ጉዳይ ላይ ሰፔሻላይዝ (Specialize) ያደረጉ ሰዎች፣ ትላልቅ ኢስላማዊ ኢኮኖሚስቶች እና ትላልቅ የፈተዋ ድርጅቶች ጉዳዩን አጥንተው ሀራም እንደሆነ ብይን ሰጥተውበታል፡፡ ከእነዚህ ወስጥ የሚከተሉት ይገኙበታል፦

1. ልጅነት ዳኢማ ሊልቡሁስ አል ዒልሚያ ወልኢፍታ ቢልመምለከቲል ዐረቢየቲ ሱዑዲያ
2.ሙጀመዐ አል ፊቅሂል ኢስላሚይ ቢሱዳን
3.ለጅነት አል ፈትዋ ቢጃሚዓተ አል አንሷረሱና አል ሙሃመዲያ ቢሚስር
4.ዶክተር አብደላ ሻኪር፣ ዶክተር ራፊዑዲን አልበደዊ፣ አል ሸይኽ ዘከሪ አል ዑሰይሚን የሚገኙበት ትልቅ የፈተዋ ተቋም
5.ዳረል ኢፍታእ ቢሀለብ
6.ለጅነት አል ፈትዋ ቢመርከዝ አል ኢማም አልባኒ ሊዲራሳት
7.መርከዝ አል ፈትዋ ቢሸበከት አል ኢስላሚያ አል ቀጠሪያ (ኢኮኖሚ ነክ ፈትዋዎችን የሚሰጡ)
8.ዶክተር ሳሊም ሱወይዲ (ኢስላማዊ ኢኮኖሚስት፣ የብዙ ኢስላማዊ ባንኮች አማካሪ እና በርካታ መጽሀፍቶችን የፃፉ)
9.ዶክተር ኢብራሂም ባሪራ (ብዙ መጽሀፍቶችን የፃፉ)
10.ዶክተር ዓሊ ሙሂዩዲን አል ቁራ
11.ዩሱፍ ዐብደላ አሹረይሚ
12.ዐብደላ አል ሩክባን
13.ዶክተር ሙሀመድ አል ዑሰይሚን
14.ሙሀመድ አል ሙነጅድ
15.ዶክተር ዑመር አል ሙቅቢል
16.ዶክተር ሁሴን አሸህራኒ
17.ሀሰን ሺበና ወዘተ

እነዚህ ሁሉም በኢኮኖሚ ጥያቄዎች ላይ ሰፔሻላይዝ ያደረጉ ተቋሞችና ሙፍቲዎች ሲሆኑ ኔትዎርክ ማርኬቲንግ ሀራም ነው ብለው ብይን ሰጥተውበታል፡፡